ሃሰተኛ ሃይማኖት ለሐዋርያት የተሰጠውን የእውነት ወንጌል ያጣምማል። ገላ1:-6-12

ሐዋርያት የሰበኩትን ኢየሱስ ሳይሆን ልዩ ኢየሱስን ልዩ መንፈስንና ልዩ ወንጌልን ይቀበላል:: 2ኛ ቆሮ 11:-1-4

*«እናንተም ከቅዱሱ ቅባት ተቀብላችኋል ሁሉንም ታውቃላችሁ:: እውነትንም የምታውቁ ስለሆናችሁ ውሸትም ሁሉ ከእውነት እንዳልሆነ ስለምታውቁ እንጂ እውነትን ስለማታውቁ አልጽፍላችሁም:: ክርስቶስ አይደለም ብሎ ኢየሱስን ከሚክድ በቀር ውሸተኛው ማን ነው? አብንና ወልድን የሚክድ ይህ የክርስቶስ ተቃዋሚ ነው:: ወልድን የሚክድ ሁሉ አብ እንኳ የለውም በወልድ የሚታመን አብ ደግሞ አለው»* የሚለውንም አይቀበልም:: 1ኛ ዮሐ. 2፡-20-23

ሃሰተኛ ሃይማኖት ሙሴ በጽላት ላይ ተጽፎ የመጣለትን የመጀመሪያ ትዕዛዝን እንኳ ይሽራል:: ትእዛዙም *«ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ»* የሚል የማይሻር አዋጅ ነው:: ዘጸ 20:-3:: ዘዳ 6:-4:: ኢሳ 43:-10-12:: 44:-6-8፤ 44:-24፤45:-5-6 ይሁዳ 3-4 ቁ 17-25

*«እስራኤል ሆይ ስማ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው አንተም አምላክህን እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ በፍጹምም ኃይልህ ውደድ»* የሚለውንም አዋጅ ንቀው በሁለትና በሦስት በዘጠኝም የሚያካፍሉት እየበዙ ናቸው:: አንዳንዱም ለአብ በግሉ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አሉት ለወልድም በግሉ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አሉት ለመንፈስ ቅዱስም በግሉ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ አሉት በማለት በሦስት መለኮት በዘጠኝ አካላት እናምናለን ይላሉ:: ይበሉ እንጅ ውሸት ስለሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ ሊያቀርቡ አይችሉም:: ዘዳ 6:-4-5 ማር 12:-29-30፤ ገላ 6:-16

እግዚአብሔር በቀናተኛነቱ ሲናገር *«አሁንም እኔ ብቻዬን እኔ እንደሆንሁ ከእኔም*



*በቀር አምላክ እንደሌለ እዩ እኔ እገድላለሁ አድንማለሁ እኔ እመታለሁ እፈውስማለሁ ከእጄም የሚያድን የለም:: እጄን ወደ ሰማይ እዘረጋለሁና እንዲሁም እላለሁ ለዘላለም እኔ ሕያው ነኝና»* ዘዳ 32:-39-40 *«ከሰማይ ከወረደው በቀር ወደ ሰማይ የወጣ ማንም የለም እርሱም በሰማይ የሚኖረው የሰው ልጅ ነው»* ዮሐ 3:-13:: የማይዋሽ አምላክ በሚከተሉት ጥቅሶች የሚያውጀውን ልብ ብለን እናስተውልና ራሳችንን እናድን::

በምሳ 19:-5 ሐሰተኛ ምስክር ሳይቀጣ አይቀ ርም በሐሰትም የሚናገር አያመልጥም:: *መዝ 5:-6*

ኢሳ 44:-25 የሐሰተኞችን ምልክት ከንቱ አደርጋለሁ ምዋርተኞችንም አሳብዳለሁ:: በዘዳ 13 ያለውን አዋጅ ልብ ብለው ይመርምሩት::

"በመካከልህም ነቢይ ወይም ሕልም አላሚ ቢነሳ፣ ምልክትም ተዓምራትም ቢሰጥህ፣ እንደ ነገረህም ምልክቱ ተዓምራቱም ቢፈጸም፣ እርሱም፦ ሄደን የማታውቃቸውን ሌሎች አማልክት እንከተል እናምልካቸውም ቢልህ፣ አምላካችሁ እግዚአብሔርም በፍጹም ልባችሁ በፍጹምም ነፍሳችሁ ትወድዱት እንደሆነ ያውቅ ዘንድ አምላካችሁ እግዚአብሔር ሊፈትናችሁ ነውና የዚያን ነቢይ ቃል ወይም ያን ሕልም አላሚ አትስማ።" ዘዳ 13፡1-3

በምሳሌ 12:-19 የእውነት ከንፈር ለዘለዓለም ትቆማለች ውሸተኛ ምላስ ግን ለቅጽበት ነው ተብሎ ተጽፎአል። *መዝ* 5:-4-10፤ ሮሜ 3:-11-18፤ ምሳ 12:-22፤ ዘካ 8:-16

በኤፌ 6:-14 «ወገባችሁን በእውነት ታጥቃችሁ የጽድቅንም ጥሩር ልበሱ» ይላልና እውነትን ይምረጡ::

Apostolische Pfingstgemeinde
Friedelsheimerstr. 18-20
D - 68199 Mannheim (Neckarau) /Germany
Pastor Raymond Wey
Assistent Pastor Sascha Wey
www.jesus-is-god.de

# *የሃሰትና የእውነት ሃይማኖት*

# የሃሰትና የእውነት ሃይማኖት በምን ይለያል?

*«ጌታ ኢየሱስ የመኑትን አይሁድ፣ እናንተ በቃሌ ብትኖሩ በእውነት ደቀመዛሙርቴ ናችሁ እውነትንም ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያወጣችኋል አላቸው»*፣ለምን ብለን ብንጠይቅ ፈሪሳውያን ከሃሰት አባታቸው ከዲያብሎስ ስለነበሩና እውነትን የሚጠሉ በተግባራቸው የእግዚአብሔር ጠላቶች በአፋቸው ግን አማኞች ስለነበሩ ነው ዮሐ8:-44-47

የእግዚአብሔር ቃል፡- *«በሃይማኖት ብትኖሩ ራሳችሁን መርምሩ ራሳችሁንም ፈትኑ... ለእውነት እንጂ በእውነት ላይ ምንም አናደርግምና»* ይላል:: 2ኛቆሮ 13:-5 ቁ 8

ሃሰተኛ ሃይማኖት ማለት ለእውነት ያልቆመ ማለት ነው:: የእግዚአብሔር ቃል፣ *«እንደ ስህተት ሽንገላ ባለ ተንኮል በሰዎችም ማታለል ምክንያት በትምህርት ነፋስ ሁሉ እየተፍገመገምን ወዲያና ወዲህ እየተንሳፈፍን ሕፃናት መሆን አይገባንም:: ነገር ግን እውነትን በፍቅር እየያዝን በነገር ሁሉ ወደ እርሱ ራስ ወደሚሆን ወደ ክርስቶስ እንደግ ስለዚህ ውሸትን አስወግዳችሁ እርስ በርሳችን ብልቶች ሆነናልና እያንዳንዳችሁ ከባልንጀሮቻችሁ ጋር እውነትን ተነጋገሩ»* ይላል:: ኤፌ 4:-14-15

በ2ኛተሰ ምዕራፍ:-2 እንደተገለጠው የዲያብሎስ ደቀመዛሙርት የሆኑት ሁሉ ውሸትን እንጂ እውነትን አይወዱም:: ፍቅርም ስለሌላቸው በውሸት ብቻ የሚንቀሳቀሱና የማይተባበራቸውን ወገን ወይም ሃይማኖት በውሸት ስሙን በማጥፋት ማጥላላትን በመዝራት የዲያብሎስን ባሕሪይ የሚያስተጋቡ ይሆናሉ:: የእውነተኛ ሃይማኖት ምልክቱ አድልዎ የሌለበት ፍቅር፣ ትህትና፣ የዋሃት፣ ገርነት መልካምነት ነው:: እውነተኛ ሃይማኖት ለነፍሳት መዳን ስለሚቆረቆር ሁሉንም በፍቅር ወደ መዳንና፣ ወደ ብርሃን፣ ወደ ጽድቅ ለማምጣት የእውነትን ወንጌል ለማሳየት እያሳየ ይጥራል እንጂ ስምን እያጠፋ በውሸት የተለወሰ ቃል በማቅረብ ሰውን ወደ ውጭ አይጥልም:: ጠላትህ ቢራብ አብላው ቢጠማም አጠጣው ይላልና ክርስቲያን ጠላት የለውም፤ መለያየት ከዲያብሎስ ስለሆነ በጽድቅ ምክንያት ኃጥዕ ቢያባርረን እንኳን በፍቅር ማሸነፍ እንጂ ሽሹ አትቅረቡአቸው በሚል በሰይጣን የፍርሃት ቃል መራቅና እንዲርቁ ማድረግ አይገባንም:: የእግዚአብሔር ቃል፣ *«የእግዚአብሔር ልጆችና የዲያብሎስ ልጆች በዚህ የተገለጡ ናቸው:: ጽድቅን የማያደርግና ወንድሙን የማይወድ ሁሉ ከእግዚአብሔር አይደለም:: ከመጀመሪያ የሰማችኋት መልዕክት እርስ በርሳችን እንዋደድ የምትል ይህች ናትና ከክፉ እንደነበረ ወንድሙንም እንደገደለ እንደ ቃየል አይደለም:: ስለምንስ ገደለው? የገዛ ሥራው ክፉ የወንድሙም ሥራ ጽድቅ ስለ ነበረ ነው:: ወንድሞች ሆይ ዓለም ቢጠላችሁ አትደነቁ:: እኛ ወንድሞችን የምንወድ ስለሆንን ከሞት ወደ ሕይወት እንደተሻገርን እናውቃለን ወንድሙን የማይወድ በሞት ይኖራል:: ወንድሙንም የሚጠላ ሁሉ ነፍሰ ገዳይ ነው ነፍሰ ገዳይም የሆነ ሁሉ የዘላለም ሕይወት በእርሱ እንዳይኖር ታውቃላችሁ::» ይላል።* 1ኛዮሐ 3:-10-17 *ወንድማችን ማን ነው? የአዳም ዘር ሁሉ። ዘሌ 19:17-18፣ ሉቃ 10:27-37።*



እርሱ (ክርስቶስ) ስለ እኛ ነፍሱን አሳልፎ ሰጥቶአልና በዚህ ፍቅርን አውቀናል እኛም ስለወንድሞቻችን ነፍሳችንን አሳልፈን እንድንሰጥ ይገባናል::

አንባቢ ሆይ! ሐዋርያው ዮሐንስ የተናገረውን መለኮታዊ እውነት አስተውል:: *«እነርሱ ከዓለም ናቸው ስለዚህ ከዓለም የሆነውን ይናገራሉ ዓለሙም ይሰማቸዋል እኛ ከእግዚአብሔር ነን እግዚአብሔርን የሚያውቅ ይሰማናል ከእግዚአብሔር ያልሆነ አይሰማንም የእውነትን መንፈስና የስህተትን መንፈስ በዚህ እናውቃለን»* ይላል:: 1ኛ ዮሐ 4:-5-6

ውሸት ኃጢአት ሆኖ ሳለ አንዳንድ ክርስቲያን ነን የሚሉ ሰዎች ውሸትን በመናገር የሃይማኖታችንን ተከታዮች አጥር እናጽና! እውነት እንዳይወሰድብን የውሸት መከላከያ እንካብ ይላሉ:: የውሸት ካብ ግን የተናደ ዕለት ያጋልጣልና እንደማያዋጣና የዲያብሎስም መርዝ መሆኑን በጊዜ ማወቁ መልካም ይሆናል::

ውሸትም ሲናገሩ ከገዛ ልባቸው ስለሚናገሩ በሕዝ. 13 የተጻፈው የመለኮት ቃል እንዲህ ያረጋግጥላቸዋል። "ከገዛ ልባቸው ትንቢት የሚናገሩትን የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ በላቸው ምን ምን ሳያዩ የገዛ መንፈሳቸውን ለሚከተሉ ለሰነፎች ነቢያት ወዮላቸው... እግዚአብሔር ሳይልካቸው እግዚአብሔር ይላል የሚሉ ሰዎች ከንቱ ነገርንና ውሸተኛ ምዋርትን አይተዋል ቃሉም ይጠና ዘንድ ተስፋ አስደርጎአል። ...ከንቱ ነገርን ስለተናገራችሁ ውሸተኛ ራእይንም ስላያችሁ ስለዚህ እነሆ እኔ በእናንተ ላይ ነኝ ይላል ጌታ እግዚአብሔር። ...ስለዚህ ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ እነሆ እኔ ነፍሳትን እንደ ወፍ በምታጠምዱበት በመከዳችሁ ላይ ነኝ ከክንዳችሁም ወስጄ እቀዳታለሁ እንደወፍም የምታጠምዱዋቸውን ነፍሳት እለቃለሁ ሽፋኖቻችሁን ደግሞ እቀዳለሁ ሕዝቤንም ከእጃችሁ አድናለሁ።



ከዚያም ወዲያ በእጃችሁ ለመታደን አይሆኑም" ሲል ቃል ኪዳን ገብቶልናል። ሕዝ. 13፡2-6 ቁ. 8-10 ቁ. 20-21። ከዚህ ምዕራፍ እንደምንመለከተው ውሸት ከሰው ልብ የሚፈልቅ ሃሳባዊነትና የንግድ፣ የጥፋት፣ የሥጋና የአጋንንትም ነው። የሚድኑትም እንዳይድኑ ወጥመድ እንደሆነ በማቴ 23፡13-15 "እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን መንግሥተሰማያትን በሰው ፊት ስለምትዘጉ ወዮላችሁ! እናንተ አትገቡም የሚገቡትንም እንዳይገቡ ትከለክላላችሁ። እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን በጸሎት ርዝመት እያመካኛችሁ የመበለቶችን ቤት ስለምትበሉ ወዮላችሁ! ስለዚህ የባሰ ፍርድ ትቀበላላችሁ። እናንተ ግብዞች ጻፎችና ፈሪሳውያን አንድ ሰው ልታሳምኑ በባሕርና በደረቅ ስለምትዞሩ በሆነም ጊዜ ከእናንተ ይልቅ ሁለት እጥፍ የባሰ የገሃነም ልጅ ስለምታደርጉት ወዮላችሁ" ይላል።

ሃሰት መራራ ጥላቻን ስለሚያስከትል ንዴትን፣ ቁጣን፣ መሳደብንና አልፎም መደባደብንና መግደልንም ስለሚያስከትል ውጤቱ እጅግ አስከፊ የገሃነም እሳት እዳ አለበት:: ወዳጄ! በየትኛው የሃይማኖት ክፍል ትገኝ ይሆን? ኢየሱስ እውነትም ሕይወትም መንገድም ነውና ወደ እውነት መንገድ ተመለስ ፍቅር የኃጢአትን ብዛት ያጠፋልና ከመራርነት ወደ ፍቅር ተመለስ።

በራእይ 21:8 የሐሰተኞች ሁሉ ዕድላቸው በዲንና በእሳት በሚቃጠል ባሕር ነው ይኸውም ሁለተኛ ሞት ነው ይላልና ከሃሰት ወደ እውነት የመውጣት ጊዜው አሁን ነው:: የፍቅር አምላክ እውነት ስለሆነ እውነትንም ብቻ ስለሚወድ የእግዚአብሔርን ባሕርይ ለመውረስ ምረጥ:: የሐሰት ነቢያትና ውሸትን እየተነበዩ ሰውን የሚያጣምሙ ሁሉ የአጋንንት ደቀመዛሙርት መሆናቸውንና ዕድላቸውም ሁለተኛው ሞት እንደሆነ የእግዚአብሔር ቃል ያረጋግጣል:: ራእይ 20:-10፣ ኤር 23:-23-36፣ ዘዳ 13:-1-18